<u>ደንብ ቁጥር 185/2017</u>

# በምሽት የንግድ እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የወጣ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ አሁን ከደረሰችበት ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ለውጥ አንፃር የአብዛኛው ማህበረሰብ የሥራ ባህል እና ፍላጎት በመለወጡ የንግድ ሥራዎችንና አገልግሎቶችን በምሽት መከወን እየተለመደ የመጣውን ተግባር ወጥነትና ቀጣይነቱን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

በከተማዋ በስፋት እየተከናወነ የሚገኘው መሠረተ-ልማት በኢኮኖሚው ላይ የፈጠረውን መነቃቃት አጠናክሮ ለማስቀጠል፣ የሥራ ባህልን ይበልጥ ለማዳበር ፣ የኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን፣ የከተማዋን ተወዳዳሪነት እውን ለማድረግ ቀን ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ በምሽት የንግድ እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በከተማዋ መንገድ ዳር ያሉ የንግድ ቤቶች እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚያበሯቸው ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ መብራቶች የአካባቢውን ውበት ይበልጥ የሚያደምቁ እና ሠላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ አጋዥ በመሆናቸው ህብረተሰቡ ለመዝናናትና እረፍት ለማድረግ የሚያዘወትራቸው ተመራጭ ቦታዎች እንዲሆኑ ለማድረግ፤

የንግድና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተቋማት በምሽት ተግባራቸውን ማከናወን የሚችሉበትን የአሰራር ሥርዓት በህግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 94 መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "በምሽት የንግድ እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የወጣ ደንብ ቁጥር 185/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ ወይም ሀረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
2. "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3. "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ነው፤
4. "ነጋዴ" ማለት ንግድን የሙያ ሥራው አድርጎ ተገቢ ጥቅም ለማግኘት በንግድ ህግ ላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎች የሚሠራ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ የንግድ ሥራ ነው ተብሎ በሕግ የሚወሰነውን ሥራ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ነው፤
5. "የንግድ ተቋም" ማለት ንግድ ሥራ ፈቃድ በማውጣት በከተማው መንገድ ዳር የንግድ ሥራ የሚሰራ የንግድ መደብር ነው፤
6. "የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋም" ማለት በከተማዋ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቶች ለመስጠት በቢሮው የተመዘገበና የኦፕሬተርነት ፈቃድ የተሰጠው የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተቋም ነው፤
7. "ምሽት" ማለት እንደአግባቡ ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ 12፡00 ሰዓት ድረስ ያለው ጊዜ ነው፤
8. "አገልግሎት ሰጪ ተቋማት" ማለት በከተማው አስተዳደር ውስጥ በመንገድ ዳር ያሉ መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ያካትታል፤
9. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤
10. በዚህ ደንብ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ፡-

1. በከተማው መንገድ ዳር በሚገኙ የንግድ ተቋማት ወይም ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ፤ እና
2. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የንግድ እና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተቋማት ግዴታ</u>

4. <u>የንግድ ተቋማት የሥራ ጊዜ</u>

ማንኛውም የንግድ ተቋም፣-

1. በቀኑ ክፍለ ጊዜ ሲካሄድ የነበረው የንግድ ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ ዘወትር ማታ ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 3፡30 ሰዓት ድረስ የንግድ ተቋሙን ለተገልጋይ ክፍት በማድረግ አገልግሎት መስጠት አለበት።
2. በምሽት ክፍለ ጊዜ የመግቢያ በሩ ዝግ በማድረግ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ የንግድ ተቋሙ ለአገልግሎት ክፍት መሆኑን የሚያሳይ በመብራት የሚሰራ ምልክት በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ ማስቀመጥ ይኖርበታል።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ከሥራ ባህሪያቸው አኳያ 24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጡ የንግድ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አይመለከትም፡፡

5. <u>የሕዝብ ትራንስፖርት ተቋማት የሥራ ጊዜ</u>

ማንኛውም የሕዝብ ትራንስፖርት ተቋም፣-

1. በቀኑ ክፍለ ጊዜ ሲያካሄድ የነበረው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንደተጠበቀ ሆኖ ዘወትር ማታ እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ከትራንስፖርት ቢሮ በሚሰጠው ስምሪት መሠረት መሰማራት ይኖርበታል፡፡

6. <u>መብራት ስለማብራት</u>

1. አግባብ ያለው የከተማው አስፈጻሚ አካል ባወጣው የመብራት ስታንዳርድ መሰረት ማንኛውም የአገልግሎት ሰጪ ተቋም፣ የንግድ ተቋም እና መኖሪያ ቤት የሕንጻ የፊተኛው ገጽ መብራት ወይም የፋሳድ ላይት መብራት ማስገባት አለበት።
2. ማንኛውም በመንገድ ዳር ላይ የሚገኝ የንግድ ተቋም ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከምሽቱ 12፡00 ጀምሮ እስከ ንጋቱ 12፡00 ሰዓት ድረስ የተቋሙን የውጭ እና የውስጥ መብራት ማብራት አለበት።



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

3. ማንኛውም በመንገድ ዳር ላይ የሚገኝ መኖሪያ ቤት ከምሽቱ 12፡00 ጀምሮ እስከ ንጋቱ 12፡00 ሰዓት ድረስ የውጭ መብራት ማብራት አለበት፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፣ (2) እና (3) ድንጋጌዎች መሠረት መብራቱ የሚሰራ መሆኑን በየዕለቱ ከመምሸቱ በፊት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

7. <u>ተገልጋይ ስለማስተናገድ</u>

ማንኛውም የንግድ ተቋም፡-

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 መሰረት በምሽት ክፍለ ጊዜ ንግድ ተቋሙን ክፍት ሲያደርግ በቀን ክፍለ ጊዜ ሲቀርብ የነበረውን አገልግሎት ወይም ምርት በተሟላ ሁኔታ በምሽት ክፍለ ጊዜም ለተገልጋይ ማቅረብ አለበት፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በባህሪያቸው ለገበያ ቀርበው ብዙ ጊዜ ሊቆዩ የማይችሉ ወይም ለማዘጋጀት ጊዜ የሚወስዱ ሸቀጦችን ወይም ምርቶችን ለማቅረብ የማይገደድ ይሆናል፤

3. በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ንዑስ (1) መሠረት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው በቀን ክፍለ ጊዜ በሚከፈለው ታሪፍ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለክልከላ እና አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

8. <u>ክልከላ</u>

1. ማንኛውም የንግድ ተቋም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድርጊቶች መፈጸም የተከለከለ ነው፡-

   ሀ) ከምሽቱ 3፡30 በፊት የንግድ ተቋሙን መዝጋት፤

   ለ) ለተገልጋይ ሊያቀርብ የሚችለው አገልግሎት ወይም ምርት እያለው የለም በማለት ተገልጋይ እንዳይስተናገድ ማድረግ፤

   ሐ) መንገድ ዳር ያሉ ንግድ ተቋማት እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ከምሽት እስከ ንጋት ድረስ የተቋሙን የውጭ እና የውስጥ መብራት አለማብራት፤

   መ) የሕንጻ የፊተኛው ገጽ መብራት ወይም የፋሳድ ላይት መብራት ያለመስቀል እና/ወይም ያለማብራት፣

   ሠ) የንግድ ተቋሙ መግቢያ በር ዝግ ሆኖ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ክፍት መሆኑን የሚያመለክት በኤሌክትሪክ የሚሰራ ምልክት ያለማድረግ፡፡

2. ማንኛውም የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድርጊቶች መፈጸም የተከለከለ ነው፦

   ሀ) ከምሽቱ 4፡00 በፊት የትራንስፖርት አገልግሎት ማቋረጥ ወይም ከስምሪት መውጣት ወይም የስምሪትን መስመር ማቆራረጥ፤

   ለ) የከተማ አስተዳደሩ ካወጣው የትራንስፖርት አገልግሎት ታሪፍ በላይ ተሳፋሪውን ማስከፈል፤

9. <u>አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

1. ማንኛውም የንግድ ተቋም ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገጉትን ክልከላዎች ተላልፎ ሲገኝ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ እንዲያስተካክል ቢሮው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ማስተካከል ካልቻለ ቢሮው ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው የቅጣት ሰንጠረዥ መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣቱን እንዲከፍል ማስታወቂያ ይሰጠዋል፤

3. የንግድ ተቋሙ በአስተዳደራዊ ቅጣቱ መታረም ሳይችል ቀርቶ በተደጋጋሚ ጥፋቶችን የሚፈጽም ከሆነ በሰንጠረዥ ላይ የተጠቀሰውን የገንዘብ ቅጣት፦

   ሀ) ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከፈጸመ 1/3 (አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል፤

   ለ) ለሶስተኛ ጊዜ ካጠፋ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) ላይ የተሰጠው ቅጣት (አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል፤

   ሐ) ለአራተኛ ጊዜ ካጠፋ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) ላይ የተሰጠው ቅጣት (አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል፤

   መ) ለአምስተኛ ጊዜ ካጠፋ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሐ) ላይ የተሰጠው ቅጣት (አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል፤

   ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት የገንዘብ ቅጣት ተቀጥቶ ማረም ካልቻለ ቢሮው የንግድ ሥራ ፈቃዱን ያግዳል፤ በእግዱ መሠረት ችግሩ ካልታረመ የንግድ ፈቃዱ ይሰርዛል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የንግድ ፈቃዱ የተሰረዘበት ሰው የንግድ ተቋሙ የንግድ ሥራ እያከናወነ የሚገኘው በመንግስት ቤት ውስጥ ከሆነ ቢሮው



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል የንግድ ሥራ ፈቃዱ የተሰረዘ መሆኑን መረጃውን ያስተላልፋል፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት መረጃው የደረሰው አስፈጻሚ አካል ቤቱን ከተከራየው ሰው ጋር ያደረገውን ውል ያቋርጣል፤ ውሉ የተቋረጠ መሆኑንም ለተዋዋዩ ያሳውቃል፤ ቤቱንም ይረከባል፤
6. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገጉትን ክልከላዎች ተላልፎ ሲገኝ በዚህ ደንብ አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣቱን እንዲከፍል ማስታወቂያ ይሰጠዋል፤
7. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በአስተዳደራዊ ቅጣቱ መታረም ሳይችል ቀርቶ በተደጋጋሚ ጥፋቶችን የሚፈጽም ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

10.<u>አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ</u>

1. በዚህ ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው የተሰጠውን አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት አካባቢ በሚገኘው የወረዳ ንግድ ጽህፈት ቤት ወይም ትራንስፖርት ቢሮ ቀርቦ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መክፈያ ዘዴ በሶስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ገንዘቡን ገቢ በማድረግ ቅጣቱን መፈጸም አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አስተዳደራዊ መቀጫውን ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት ገንዘብ መጠን እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል፤
3. የቅጣት ማስታወቂያ ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ እንደተቀበለ ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤
4. ቢሮው ወይም የትራንስፖርት ቢሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት መቀጫውን ገቢ ያላደረገ ማንኛውም ሰው ላይ ክስ እንዲቀርብ ለከተማው አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ማስረጃውን አደራጅቶ ይልካል፡፡

Addis Ababa City Administration Justice Bureau

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

11. ቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ

1. ቢሮው ወይም የትራንስፖርት ቢሮ በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ውሳኔው በተሰጠው በሦስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታው ውሳኔውን ለሰጠው አስፈጻሚ አካል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፤
2. ቅሬታውን የተቀበለው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በሚኖሩት 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳቡን ለቢሮው ወይም ለትራንስፖርት ቢሮ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ አለበት፤
3. የውሳኔ ሀሳብ የቀረበለት የበላይ ኃላፊ በ5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤
4. የበላይ ኃላፊው የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፤
5. ቅሬታ አቅራቢው ላቀረበው ቅሬታ ውሳኔ እስከተሰጠ ድረስ ቅጣቱ ከመፈጸም ታግዶ ይቆያል፤
6. የአስፈጻሚ አካሉ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡

12. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈጸም ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

13. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የከተማ ካቢኔ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

14. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከየካቲት 29 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት 29 ቀን 2017ዓ.ም

አዳነች አቤቤ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

## አባሪ፡ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የጥፋቱ ዓይነት | የቅጣት ክፍያ ለአንድ ጊዜ ጥፋት በብር መጠን |
|---|---|---|
| 1 | ከምሽቱ 3፡30 በፊት የንግድ ተቋሙን መዝጋት፤ | 10,000.00 |
| 2 | ለተገልጋይ ሊያቀርብ የሚችለው አገልግሎት ወይም ምርት እያለው የለም በማለት ተገልጋይ እንዳይስተናገድ ማድረግ፤ | 10,000.00 |
| 3 | መንገድ ዳር ያሉ ንግድ ተቋማት እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ከምሽት እስከ ንጋት ድረስ የተቋሙን የውጭ እና የውስጥ መብራት አለማብራት፤ | 7,000.00 |
| 4 | የሕንጻ የፊተኛው ገጽ መብራት ወይም የፋሳድ ላይት መብራት ያለመስቀል እና/ወይም ያለማብራት፣ | 5,000.00 |
| 5 | የንግድ ተቋሙ መግቢያ በር ዝግ ሆኖ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ክፍት መሆኑን የሚያመለክት በኤሌክትሪክ የሚሰራ ምልክት ያለማድረግ፡፡ | 5,000.00 |
| 6 | ከምሽቱ 4፡00 በፊት የትራንስፖርት አገልግሎት ማቋረጥ ወይም ከስምሪት መውጣት ወይም የስምሪትን መስመር ማቆራረጥ፣ | 5,000.00 |
| 7 | የከተማ አስተዳደሩ ካወጣው የትራንስፖርት አገልግሎት ታሪፌ በላይ ተሳፋሪውን ማስከፈል፡፡ | 5,000.00 |

Addis Ababa ... Administration Justice Bu...